የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ገንዘብ ቢሮ

የካፒታል ሀብቶችን የማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር

178/2018



ጳጉሜ 2018 ዓ.ም

ባህር ዳር

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ

የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 178/2018

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 99 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 162/2008 አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የካፒታል ሃብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 178/2018 ዓ.ምተብሎ" ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በገቢ ግብር አዋጁ እና በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-

1/ "ቢሮ" ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ማለት ነው፡፡

2/ "የገቢዎች ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ መምሪያዎችን፣ጽ/ቤቶች እና የቀበሌ ማእከላትን ይጨምራል፡፡

3/ "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ነው፡፡

4/ "ግብር የሚከፈልበትን ሃብት በማስተላለፍ የተገኘ ጥቅም" ማለት ሃብቱን በማስተላለፍ የተገኘው የገንዘብ መጠን ሃብቱ በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ በልጦ የተገኘው የገንዘብ መጠን ሲሆን፣ መብትን ወይም ምርጫን በማስተላለፍ የሚገኝን ጥቅም ይጨምራል፤

5/ "ምድብ 'ሀ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት" ማለት በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 56(7)(ለ) እና አንቀጽ 2(13) መሰረት የማይንቀሳቀስ ሀብት ሲሆን በማዕድን ወይም በነዳጅ ሀብት ላይ ያለን መብት ወይም የማዕድን ወይም የነዳጅ መረጃዎች ይጨምራል፤

6/ "ምድብ ለ ግብር የሚከፈልበት ሀብት" ማለት በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 56(7) (ሐ) ላይ በተገለጸው መሰረት አክስዮኖችና ቦንዶች ናቸው፤

7/ "ለሀብት የሚደረግ ወጪ" ማለት በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 65 ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

8/ "ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 67 ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

9/ "አክሲዮን ማስተላለፍ" ማለት በአክሲዮን ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወይም የሽርክና ማህበር ውስጥ ባለ አክስዮን የነበረ ሰው አክስዮኑን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ ነው፡፡

10/ "ደንብ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 162/2010 ነው፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የምድብ 'ሀ' እና የምድብ 'ለ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት በማስተላለፍ ጥቅም በሚያገኙ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የካፒታል ሀብቶች በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር ስለመክፈል

4. የግብር መጣኔ

በአዋጁ አንቀጽ 56 በተደነገገው መሰረት አንድ ሰው በምድብ 'ሀ' ወይም በምድብ 'ለ' የተጠቀሱ ሀብቶችን በማስተላለፍ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በተገኘው ጥቅም ላይ እንደቅደም ተከተላቸው 15 በመቶ ወይም 30 በመቶ ግብር ይከፍላል።

5. የግብር ስሌት

1/ በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት አንድ የንግድ ስራ ሀብት በአዋጁ አንቀጽ 56 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ ፣የንግድ ስራ ሀብቱን በማስተላለፍ ከተገኘው ገቢ ውስጥ ከንግድ ስራው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው ለንግድ ስራ ሀብት የተደረገው ወጪ በንግድ ሥራው ገቢ ውስጥ የሚካተት ሲሆን፣የንግድ ሥራው ሀብት በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ በልጦ የተገኘው መጠን በዚህ መመሪያ መሠረት ግብር ይከፈልበታል፤

2/ በአዋጁ አንቀጽ 56 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሙሉ ለሙሉ ለቤት ኪራይ አገልግሎት ውሎ የነበረ እንደሆነ ሀብቱን በማስተላለፍ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ ለሀብቱ የተደረገው ወጪ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን በቤት ኪራይ ገቢ ውስጥ የሚካተት ሲሆን፣ ለሀብቱ ከተደረገው ወጪ በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአዋጁ አንቀጽ 56 እና በዚህ መመሪያ መሰረት ግብር ይከፈልበታል፤

3/ የካፒታል ሀብትን በማስተላለፍ ከተገኘው ጠቅላላ ጥቅም ውስጥ በንግድ ስራ ገቢ ወይም በቤት ኪራይ ገቢ ወይም ለሁለቱ አገልግሎት የሚካተተው እና በአዋጁ አንቀጽ 56 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ መጠን ቀጥሎ በተመለከተው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፤

ረ= ሀ-(ለ+መ)

ሠ= ለ-ሐ

ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፡-

ሀ- ሀብቱ የተሸጠበት ዋጋ

ለ- ሀብቱ የተገኘበት /የተገዛበት ዋጋ (ለሀብቱ የተደረገ ወጪን ጨምሮ)

ሐ- የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ

መ- የግሽበት ማስተካካያ

ሠ- ከሀብቱ ሽያጭ የተገኘ ጠቅላላ ጥቅም ወይም ኪሳራ የንግድ ስራ ገቢ ወይም/እና የቤት ኪራይ ውስጥ የሚካተት ገቢ

ረ- ከሀብቱ ሽያጭ ከተገኘ ጥቅም የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ ግብር የሚከፈልበት ገቢ

4/ ግብር የሚከፈልበት ሀብት ለንግድ ስራ እና ለኪራይ አገልግሎት ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለሀብቱ የተደረገው ወጪ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን ሀብቱ በተሸጠበት ጊዜ ለንግድ ስራ እና ለኪራይ አገልግሎት በዋለው መጠን ልክ ተከፋፍሎ በንግድ ስራ ገቢ እና በቤት ኪራይ ገቢ ውስጥ የሚካተት ሲሆን፣ ሀብቱ ከተደረገው ወጪ በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአዋጁ አንቀጽ 56 እና በዚህ መመሪያ መሰረት ግብር ይከፈልበታል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም በደንቡ አንቀጽ 57(1) መሰረት የሚተላለፈው የምድብ 'ሀ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲሆን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማስላት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ይደረጋል፤

6/ የምድብ 'ለ'ግብር የሚከፈልበት ገቢን ለማስላት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ተፈጻሚ አይሆንም፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የሚደረገው የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ በበጀት አመቱ ስራ ላይ ውሎ የነበረውን ባንኮች በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፍሉትን ወለድ አማካይ መጣኔ መሰረት በማድረግ ይወሰናል፤

8/ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ የሚቀነሰው በሠንጠረዥ 'ሐ' ወይም/ እና 'ለ' መሰረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከተለየ በኋላ ነው።

6. <u>የንግድ ድርጅት ሲተላለፍ ሊቀርብ ስለሚገባ ሰነድ</u>

1/ የንግድ ድርጅት በሚተላለፍበት ጊዜ ከድርጅቱ ጋር አብረው የሚተላለፉ ሀብቶችች ዝርዝር የመዝገብ ዋጋ በግልፅ መቅረብ አለበት፤

2/ ግብር ከፋዩ የሚተላለፉ ሀብቶች ዝርዝር ዋጋ ለይቶ ማቅረብ ካልቻለ አግባብነት ባለው ሀብት ገማች የተገመተ ሀብቱ የተገዛበት ዋጋ ማቅረብ ይኖርበታል።

7. <u>ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢን ለማስላት መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች</u>

1/ የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ ለካፒታል ሀብቱ የተደረገውን ወጪ የሚከተሉትን ማስረጃዎች በማቅረብ ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) ለሀብቱ የተደረገውን ወጪ እና ሀብቱ የተገኘበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰነድ፣

ለ) ሀብቱ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ስለእርጅና በጠቅላላው ተቀናሽ የተደረገውን ገንዘብ የሚያስረዳ ሰነድ

2/ ግብር ከፋዩ ሀብትን በማስተላለፍ ያገኘውን ገቢ አግባብነት ባለው ማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን፤ በቀረበው ማስረጃ መሰረት ግብሩ የሚከፈለው ማስረጃው በገቢዎች ቢሮ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፤

3/ ለካፒታል ሀብቱ ስለተደረገውን ወጪ እና የካፒታል ሃብቱን በማስተላለፍ ስለተገኘው ገቢ በግብር ከፋዩ የቀረበው ማስረጃ በገቢዎች ቢሮ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 3 መሰረት የካፒታል ሀብትን በማስተላላፍ የተገኘው ጥቅም ይሰላል፤

4/ የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም እንዲይዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ሀብቱ የተገኘበትን ዋጋ በሚመለከተው አካል አስገምቶ እንዲያቀርብ ይደረጋል። ሆኖም ግብር ከፋዩ ይህን አስገምቶ ካላቀረበ ግብር ከፋዩ ወጪ እንደሌለው ይቆጠራል፤

5/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም 'አግባብነት ያለው ማስረጃ' ማለት የጸደቀ ውል ሲሆን በውሉ ላይ የተጠቀሰው የመሸጫ ዋጋ ተቀባይነት የሚያገኘው ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ሲገኝ ነው።

8. በቤት አልሚዎች የሚተላለፍ ቤት

ቤት ገንብተው በሚሸጡ የቤት አልሚዎች ላይ መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆነው አስቀድሞ የቤቶቹ ባለቤትነት በቤት አልሚው ስም የተመዘገበ እንደሆነ ብቻ ነው።

9. የማይንቀሳቀስ ሀብት ስለማስተላለፍ

1/ ግንባታው ያልተጠናቀቀ ወይም ሁለት አመት በመኖሪያነት ያላገለገለ የማይንቀሳቀስ ሃብት በማስተላለፍ ከሚገኝ ጥቅም ላይ በአዋጁ መሰረት 15 በመቶ ግብር ይከፈልበታል፤

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም የማይንቀሳቀስ ሃብት ፕላን የመኖሪያ ቤት የሚል ቢሆንም በቤት ቁጥሩ ንግድ ፈቃድ የወጣበትና ለንግድ አገልግሎት ሲውል የነበረ ከሆነ በአዋጁ መሰረት 15 በመቶ ግብር ይከፈልበታል።

10. የኩባንያዎች የአክስዮን ሽያጭ ገቢ

ኩባንያዎች ያወጡትን አክስዮን ከዋጋው በላይ በመሸጥ የሚያገኙት ገቢ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት ሲሆን፣ በአዋጁ አንቀጽ 61(1)ሀ መሰረት ይህ ጥቅም የካፒታል ሀብቶችን በማስተላላፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚጣለው ግብር ተፈጻሚ አይደረግበትም።

11. ለባንክ ዕዳ መክፈያ ስለተያዘ የማይንቀሳቀስ ሃብት

1/ ባንኮች በዋስትና የያዙትን የማይንቀሳቀስ ሃብት ለብድር ዕዳ ማስመለሻ በሚያውሉበት ወቅት ንብረቱ ሲሸጥ ሊከፈል የሚገባው የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ተፈጻሚ የሚሆነው ከንብረቱ ሽያጭ የተገኘው ገቢ ባንኮች የሰጡትን የብድር ገንዘብ ከሸፈነ በኃላ ቀሪ ገንዘብ ካለ ብቻ ነው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባንኮች የቅድሚያ መብት የሚኖራቸው በታክስ አስተዳደር አዋጅ 241/2008 አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው ሀብቶች ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ እዳ የሌለበት መሆኑ ከገቢዎች ቢሮ ክሊራንስ ለባንኩ ተጽፎ ከሆነ ብቻ ነው።

12. ሀብትን በስጦታ ስለማስተላለፍ

'ምድብ 'ሀ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት ወይም 'ምድብ 'ለ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት በስጦታ ሲተላለፍ ስጦታ ተቀባዩ የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ይከፍላል። ግብሩ የሚሰላው በደንቡ አንቀጽ 53 መሠረት በስጦታ ከተላለፈው ሀብት የገበያ ዋጋ ላይ ለሀብቱ የተደረገው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ በሚቀረው የገቢ መጠን ላይ ነው።

13. ሀብትን በውርስ ስለማስተላለፍ

'ምድብ 'ሀ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት ወይም 'ምድብ 'ለ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት በውርስ ሲተላለፍ የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ላይ ግብር አይከፈልበትም።

14. ሀብትን በማስተላለፍ በሚገኝ ገቢ ላይ የግብር አከፋፈል ሁኔታ

የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 44 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣'ምድብ 'ሀ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት ወይም 'ምድብ 'ለ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲተላለፍ ግብር ከፋዩ ሊከፈል የሚገባን ግብር በቀጥታ ለገቢዎች ቢሮ ማስገባት ይኖርበታል።

15. ዕጣን ወይም ድርሻን ስለማስተላለፍ

በሕብረት ስራ ማህበር ውስጥ ያለን ዕጣ ወይም ድርሻ በሚተላለፍበት ጊዜ የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ተፈጻሚ አይሆንም።

16.በወረዳ ከተሞችና ሳታላይት ከተሞች ስለሚገኝ የማይንቀሳቀስ ሀብት

መመሪያው በከተማ አገልግሎት ተፈጻሚ የሚደረገው በተመሳሳይ መንገድ በወረዳ ከተሞች እና ሳታላይት ከተሞች ላይም ለማድረግ የካፒታል ሀብቶች በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ በመመሪያው አንቀጽ 6 እና ተከታዮቹ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

17.የሽያጭ/የስጦታ/የልውውጥ ውል መፍረስ

1/ 'ምድብ 'ሀ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት ወይም 'ምድብ 'ለ' ግብር የሚከፈልበት ሀብትን ለመሸጥ/በስጦታ ለመስጠት/ለመለዋወጥ የተደረገው ውል ሲፈርስ የካፒታል ሃብት በማስተላልፍ ከሚገኝ ገቢ ላይ የተከፈለው ግብር ተመላሽ ይደረጋል። ሆኖም ግብር

ከፋዩ የከፈለው ግብር ተመላሽ እንዲደረግለት ለገቢዎች ቢሮ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ግብሩ ከተከፈለ በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሉ መፍረሱን በሚመለከተው መስሪያ ቤት ማረጋገጫ በ10 ቀናት ውስጥ ካላቀረበ በህጉ እንዲከፍል ግዴታ የተጣለበትን ግብር ይከፍላል፡፡

ክፍል ሶስት

ልዩ ድንጋጌዎች

18. የአሰራር ሥርዓት ስለመዘርጋት

ስለትክክለኛ የዕቃ ወይም የአገልግሎት የገበያ ዋጋ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት ገቢዎች ቢሮ ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የሚረዳ የአሰራር ሥርዓት እንደአስፈላጊነቱ ሊዘረጋ ይችላል፡፡

19.የመሸጋገርያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመጽናቱ በፊት የካፒታል ሀብቶች በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ቅሬታ ላይ ያሉ ወይም ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናሉ፡፡

20.የተሻረ መመሪያ

የገቢዎች ቢሮ የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣው መመሪያ ቁጥር ገባ 10/2001 ዓ.ም በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

21.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከጸደቀበት .....ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ መመርያው እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ ያለ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ዉጤት የሚኖረው መመርያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአብክመ ገንዘብ ቢሮ ድረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ጥላሁን መሀሪ አንተነህ(ዶ/ር)

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ኃላፊ